# በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የማማከር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1005/2016

Environmental and Social Impact Assessment Consulting Service Qualification Certification Directive No. 1005/2016

የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
Ethiopian Environmental Protection Authority

ሰኔ 5፥ 2016

ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ዘለቄ ልማትን ለማረጋገጥና የዜጎችን በንፁህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መከናወን ያለበት በመሆኑ፣

አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅዕኖችን ለመተንበይ እና ለመለየት የሚከናወኑ ጥናቶች ጥራት ያላቸው እንዲሆኑ፤ ሙያዊ ብቃት እና የሙያ ስብጥር ባላቸው ባለሙያዎቸ እንዲጠኑ በማድረግ በልማት ውጥኖች እና ተግባራት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ፣

በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በስልታዊ የአካባቢ ግምገማ እና በአካባቢ ኦዲት የማማከር አገልግሎት የሚሰማሩ ባለሙያዎችን እና ድርጅቶችን እውቅና ለመስጠት እና ለመቆጣጠር የሚያስችል መመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀት ወጥነትና ተጠያቂነት ያለው የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር በአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19(4) እና በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 አንቀፅ 7(2) እና አንቀፅ 20 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የማማከር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር** 1005/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ፦

1/ "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማለት ነዉ፤

2/ "አመልካች" ማለት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት የማማከር አገልግሎት ላይ በባለሙያነት ወይም በአማካሪ ድርጅትነት ለመመዝገብ ያመለከተ ሰው ነው፤

3/ "አማካሪ ድርጅት" ማለት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት ለማከናወን በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሠጠው ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

4/ "ባለሙያ" ማለት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት ላይ የማማከር አገልግሎትን ለመስጠት በባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ የተሠጠው ሰው ነው፤

5/ "ሰርተፊኬት" ማለት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት ላይ የማማከር አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ወይም አማካሪ ድርጅቶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ነው፤

6/ "መዝገብ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት የማማከር አገልግሎትን ለመስጠት የተመዘገቡ ባለሙያዎች እና የአማካሪ ድርጅቶች መረጃ የያዘ ቋት ነው፤

7/ "የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን" ማለት በየክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ተግባር ሃላፊነት እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው ተቋም ነው፤

8/ "የአካባቢ ኦዲት" ማለት የአካባቢና ማህበራዊ ጥበቃን ለማረጋገጥ የአንድ ፕሮጀክት፣ ድርጅት ወይም መሳሪያ ውጤታማነትን ለመገምገም የሚደረግ ስልታዊ፣ የተሰነደ፣ ወቅታዊ እና ተጨባጭ የሆነ ግምገማን የሚያካትት የአካባቢ እና ማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ነው፤

9/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ፣ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት የማማከር አገልግሎት ላይ በሚሰማሩ ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች በመላ ሀገሪቱ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት የማማከር አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የሚያሥችል መመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀት የሚደረጉ ጥናቶች እና የሚዘጋጁ ሰነዶች ጥራትን በማስጠበቅ የአካባቢ ደህንነት መብቶችና አላማዎችን ማስከበር ነው፡፡

5. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ደረጃዎች

1) የብቃት ማረጋገጫ ሰጃዎች በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

ሀ) ጀማሪ የብቃት ማረጋገጫ፤

ለ) መካከለኛ የብቃት ማረጋገጫ፤

ሐ) ከፍተኛ የብቃት ማረጋገጫ

## ክፍል ሁለት
## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

### 6. አዲስ የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚጠይቅ ባለሙያ በባለስልጣኑ፣ በክልል፣ ዞንና ወረዳ እንዲሁም በከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ውስጥ በቋሚ ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የማይሰራ መሆን አለበት፤

2/ ማንኛውም አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚፈልግ ሰው ባለስልጣኑ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የሚከሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

ሀ) በዕዝል ሁለት በተመላከተው የሙያ ዝርዝር ወይም ከውጪ ሀገር የተገኘ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የአቻ ግምት ማስረጃ ከዲግሪ ያነሰ ያልሆነ የሚያረጋግጥ የትምህርት መስረጃ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

ለ) ባመለከተበት የስራ መስክ ቢያንስ የአምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

ሐ) በሙያው እንዳያገለግል የሚከለክል የሕግ እገዳ የሌለበት ስለመሆኑ፤

3/ በዕዝል 1 ከተዘረዘሩት የሥራ ልምዶች ከሚያሟሉ ማንኛዉም ባለሙያዎች በስተቀር ማግኘት የሚችሉት የጀማሪነት አማካሪ ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትይሆናል፣

4/ በዚህ መመሪያ መሰረት በአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት የሚሰማራ አማካሪ ባለሙያ ደረጃ በእዝል 3 በተዘረዘሩት ተፈላጊ መስፈርቶች መሰረት የሚወሰን ይሆናል።

### 7. የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ደረጃን ለማሳደግ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳደግ የሚፈልግ ሰው ባለስልጣኑ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የሚከሉትን መረጃዎች አያይዞ በማቅረብ፡-

1/ ከጀማሪ ባለሙያ ወደ መካከለኛ ደረጃ ለማሳደግ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው የቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሠጠው ከሶስት ዓመት በኂላ ነው፤

2/ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ባለሙያ ለማሳደግ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው የቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሠጠው ከሁለት ዓመት በኂላ ነው፤

3/ ከጀማሪ ወደ መካከለኛ ለማሳደግ የጀማሪነት አማካሪነት ከተሰጠው በኂላ ሰርቶ ስላጠናቀቃቸው አራት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ስራዎች ዝርዝር የሚገልፅ ጥናቱ ከፀደቀበት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፤

4/ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ለማሳደግ የመካከለኛ አማካሪነት ከተሰጠው በኂላ ሰርቶ ስላጠናቀቃቸው ሶስት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት

ስራዎች ዝርዝር የሚገልፅ ጥናቱ ከፀደቀበት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት የተረጋገጠ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል ፤

5/ የቀድሞውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመያዝ መቅረብ አለበት።

## 8. የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት፣ የቀድሞውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በመያዝ መቅረብ አለበት፤

2/ ሰርቶ ስላጠናቀቃቸው የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ስራዎች ዝርዝር የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

3/ የባለሙያ የምስክር ወረቀት ፈቃድ ከተሠጠበት ቀን ጀምሮ በየሶስት ዓመት ቀርቦ መታደስ አለበት፤

4/ የምስክር ወረቀት የእድሳት የጊዜ ገደብ ከማለፉ ከአንድ ወር ጊዜ ጀምሮ ለማሳደስ ማቅረብ ይኖርበታል፤

5/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ ባለሙያ በሁለት ወራት ውስጥ በመቅረብ በቅጣት ይታደስለታል፣

6/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት ፈቃዱን ያለሳደሰ ባለሙያ የምስክር ወረቀቱ እንደታገደ ይቆጠራል።

## 9. አዲስ የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ ማንኛውም አዲስ የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚፈልግ ሰው ባለስልጣኑ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና የሚከተሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፦

ሀ) አማካሪ ድርጅት ለሚያመለክተው ደረጃ በዚህ መመሪያ በዕዝል 4 የተዘረዘሩትን የመመዘኛ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፤

ለ) የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀረበው ድርጅት ባለቤቶች ከአንድ ግለሰብ በላይ ከሆኑ ስልጣን ባለው አካል የፀደቀ የድርጅት መመስረቻ ሰነድ፣ መተዳደሪያ ደንብ እና ማመልከቻውን ይዞ የቀረበው ግለሰብ የውክልና ማስረጃ፤

ሐ) ከተፃፈ አንድ ወር ያልሞላው የባንክ መግለጫ ፤

2/ አዲስ የምስክር ወረቀት ለመረከብ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ወይም ሌላ ውክልና ያለው ሰው በግንባር መቅረብ አለበት።

## 10. የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከደረጃ ሁለት ወደ ደረጃ አንድ ለማሳደግ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደግ የሚቀርብ ጥያቄ በባለስልጣኑ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና ከሚከተሉትን መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የቀድሞውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፤

ሐ) ጥያቄው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክለና ማስረጃና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት

መ) ለተጠየቀው ደረጃ በዚህ መመሪያ መሰረት እንዲሟሉ የሚፈልጉ ባለሙያዎች የታደሰ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤

2/ ማንኛውም አማካሪ ድርጅት የደረጃ እድገት ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው የቀድሞ የአማካሪነት ደረጃ ከተሠጠው ከሶስት ዓመት በኋላ ነው፣

3/ ማንኛውም አማካሪ ድርጅት የደረጃ እድገት ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው የቀድሞ የአማካሪነት ደረጃ ከተሠጠው በኋላ አምስት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የአካባቢ ኦዲት ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ሰነድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

## 11. የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚፈልግ ድርጅት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና የሚከተሉትን መረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የቀድሞውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በመያዝ መቅረብ አለበት፤

ለ) ከሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት የዘመኑን ግብር መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና የታደሰ የንግድ ፈቃድ፤

ሐ) የታደሰ የባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

መ) ከሥራ የተሰናበተ ነባር ባለሙያ ካለ በሌላ ባለሙያ የተተካበትን ወይም የተቀጠረበትን የውል ስምምነት ሰነድ፤ ፤

2/ የድርጅት የምስክር ወረቀት ፈቃድ ከተሠጠበት ቀን ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ ቀርቦ መታደስ አለበት፡፡

## 12. የውጪ ሀገር ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች

1/ ማንኛውም የውጪ ሀገር አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ በማማከር አገልግሎት ላይ ለመሰማራት ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል፤

2/ ማንኛውም የውጪ ሀገር አማካሪ ድርጅት በማማከር አገልግሎት ላይ ለመሰማራት የሚችለው በሀገሪቱ ውስጥ ፈቃድ ከተሠጠው አማካሪ ድርጅት ጋር ጥምረት በመመስረት ብቻ ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 ሥር የተጠቀሰው እደተጠበቀ ሆኖ በሀገሪቱ ውስጥ ካለ አማካሪ ድርጅት ጋር በጥምረት ለመስራት ውል ከመግባቱ በፊት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 13. የባለሙያዎች እና የአማካሪ ድርጅቶች ተሳትፎ

1/ አንድ ባለሙያ በመመሪያው የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት ከሁለት የሙያ ዘርፎች በላይ ፈቃድ ሊወስድ አይችልም፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ባለሙያ በአንድ ጥናት ላይ ሊሳተፍ የሚችለው በአንዱ የሙያ ፈቃድ ብቻ ነው፤

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአማካሪው ድርጅት በቀረበው ቢ.ጋር መሰረት በባልስጣኑ ይሁንታ ሲሰጠው በሁለት ዘርፍ ላይ በአንድ የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም በአካባቢ ኦዲት ሊሳተፍ ይችላል ፡፡

4/ ማንኛውም ድርጅት ወይም ባለሙያ ባዘጋጀው የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ላይ በሚደረግ የአካባቢ ኦዲት ላይ ማሳተፍ አይችልም፡

5/ አማካሪ ድርጅቶች እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ ከተዘረዘሩት ባለሙያዎች የሙያ ዘርፍ ዉጪ ተጨማሪ ባለሙያ ሲያስፈልጉ በባለስልጣኑ በማሳወቅ ማሳተፍ ይችላሉ፤

6/ የአማካሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ለመስራት የሚፈልግ ሰው ቢያንስ የመካከለኛ አማካሪ ደረጃ የባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

7/ በፕሮጀክት ባለቤቱ ወይም ፕሮጀክቱን በሚተገብረው ሴክተር መ/ቤት ውስጥ የሚሰራ ማንኛውም ባለሙያ በሚጠናው የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም በአካባቢ ኦዲት ስራ መሳተፍ አይችልም፡፡

## 14. ስለ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ይዘት

1/ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ያሟላ አመልካች ከሰባት የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2/ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚሠጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) የባለሙያውን ወይም የድርጅቱን ሙሉ ስም፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሠጠበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ፤

ሐ) የምስክር ወረቀቱ ደረጃ፤

መ) የምስክር ወረቀቱ የተሠጠበት ቀን፤

ሠ) የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ፤

ረ) የባለሙያውን ወይም የድርጅቱን ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ፍቶ ግራፍ

ሰ) በባለስልጣኑ የሚሰጥ መለያ ቁጥር

ቀ) የፈቃድ ሰጪውን ኃላፊ ሥም፣ ፊርማና የባለስልጣኑ መ/ቤት ማህተም

## 15. የጠፋ ወይም የተበላሸ የምስክር ወረቀትን ስለመተካት

1/ የምስክር ወረቀቱ ዋና ቅጂ ከጠፋ ወይም ከተበላሸ አመልካቹ ለዚሁ ተግባር በባለስልጣኑ የተዘጋጀ ቅፅ ሞልቶ በምትኩ ሌላ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ባለስልጣኑ መጠየቅ ይችላል፤

2/ የጠፋ የምስክር ወረቀትን ለመተካት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር አግባብ ካለው የሕግ አስፈፃሚ አካል መጥፋቱን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

3/ የምስክር ወረቀቱ መጥፋቱ ከተረጋገጠ በምትኩ ሌላ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

4/ የተበላሸ የምስክር ወረቀት እንዲተካለት የሚጠይቅ ሰው የተበላሸውን ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል፤

## 16. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድ

1/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊታገድ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መፈፀማቸውን ሲረጋገጥ ይሆናል፤

ሀ) ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር በመጣስ ስራውን ተገቢ ባልሆነ አሠራር ያከናወነ ሲሆን፤

ለ) ለባለስልጣኑ እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ሪፖርቶች ወይም መረጃዎች ሳይቀርብ ሲቀር፤

ሐ) የሌላ ሰውን ስራ የራሱ አስመስሎ የቀዳ ወይም የገለበጠ እንደሆነ፤

ሠ) በአንቀፅ 14 (5) መሰረት በባለስልጣኑ ፈቃድ ከተሰጣቸው በስተቀር የአማካሪነት ፍቃድ የሌላቸዉን ባለሙያዎች በአካባቢያዊና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግማገማ፣ በስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም በአካባቢ ኦዲት ሰነድ ዝግጅት ላይ አሳትፎ ሲገኝ፤

ረ) ፈቃድ ባላገኘበት የማማከር ደረጃ ተሰማርቶ ከተገኘ፤

ሰ) በአካባቢያዊና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግማገማ፣ በአካባቢ ኦዲት ወይም በስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ዘገባዉ ዉስጥ ሀሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ፤

ሸ) ቢሮ የሌላቸው አማካሪ ድርጅቶች ወይም የቢሮ ቅያሪ ማድረጋቸዉን አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ካላሳወቁ ወይም በዚህ መመሪያ በዕዝል 3 የተቀመጠዉን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟላ ከሆነ፣

ቀ) በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ ግዴታና ሃላፊነቶች ሳይወጣ ሲቀር፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑሥ አንቀፅ 1 መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ባለሙያ ወይም ድርጅት ላይ የእገዳ እርምጃው የሚቆየው እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፤

3/ እገዳው ሊነሳ የሚችለው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱትን ጉድለቶች መስተካከላቸው ወይም ሊታረሙ የሚችሉ መሆናቸውን በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ ይሆናል::

## 17. የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

1/ የምስክር ወረቀት ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፤

ሀ) ምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወይም በራሱ ጥያቄ ወይም በሌላ ምክንያት ስራውን ሲተው፤

ለ) አመልካቹ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማጭበርበር መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ሐ) የምስክር ወረቀቱ ከህግ አግባብ ውጪ ለሌላ ሰው ተላልፎ ከተገኘ፤

መ) የምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት መክሰሩ ወይም መፍረሱ አግባብነት ባለው ፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ወይም በራሱ ምክንያት ስራውን አቁሞ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስ፤

ሠ) ባለሙያ ወይም አማካሪ ድርጅት ከአንድ ጊዜ በላይ እገዳ የተጣለበት ከሆነ፤

ረ) አንድ ባለሙያ በአንድ ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ ለሁለት እና ከዚያ በላይ ድርጅት ዉስጥ በዋና መስራችነት ተሳትፎ ወይም ውል ገብተዉ ሲገኝ፤

ሰ) አማካሪ ድርጅቱ ባልተሳተፈበት የጥናት ሰነድ ላይ በድርጅቱ እውቅና የተቋሙ ማህተም ሲገኝ፤

ሽ) የምስክር ወረቀቱን ያሳገዱ ምክንያቶች እገዳው በተጣለ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተስተካከሉ ወይም በሚመለከተው አካል እገዳው እንዳይነሳ ሲወሰን፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው የምስክር ወረቀቱን በአስር የስራ ቀናት ውስጥ የመመለስ ግዴታ አለበት።

## 18. ስለውክልና

አዲስ ወይም ምትክ የምሰክር ወረቀት እንዲሰጥ እንዲሁም እንዲታደስ ወይም የደረጃ እድገት እንዲደረግ የሚቀርብ ጥያቄን ከምስክር ወረቀት ያገዙ በተሰጠ ህጋዊ ውክልና ካልሆነ በስተቀር ማስፈፀም አይቻልም።

## 19. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

1/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ለማሳደስ ወይም ለማሳደግ የቀረበ ማመልከቻ በባለስልጣኑ ውድቅ በመደረጉ ወይም የምስክር ወረቀቱ በመሰረዙ ወይም አይሻሻልም በመባሉ ወይም በማናቸውም ምክንያት ማመልከቻው ውድቅ በመደረጉ ቅር የተሰኘ አመልካች ሁኔታው በጽሑፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቅሬታውን ማመልከቻ ሊያቀርብ ያልቻለ ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ በተወገደ በ 3 ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ ይችላል።

3/ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ውጤቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር በ 7 የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ ያለበት ሲሆን ዋና ዳይሬክተሩም በቅሬታው ላይ በ 5 የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት አለበት ።

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት በዋና ዳይሬክተሩ የተሰጠ ውሳኔን በሚመለከት በሕግ አተረጓጎም ስህተት ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠ በ 60 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. መሸጋገሪያ ደንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው የብቃት ማረጋገጫ የተሠጣቸው ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች ይህ መመሪያ በፀደቀ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በመመሪያው መሰረት የሚጠበቅባቸውን በሟሟላት መመዝገብ ይኖርባቸዋል ፡፡

### 21. የመመሪያው ትግበራ

1/ የክልል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተሰጣቸው የሙያ ፈቃድ መሰረት ተግባራቸውን የማያከናውኑ ባለሙያዎች ወይም ድርጅቶች ሲያገኙ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

2/ ባለስልጣኑ በመመሪያው አፈፃፀም ላይ የሚነሰሱ ጉዳዮች ላይ የሚያማክር ቴክኒካል ኮሚቴ በዕዝል 2 በተቀመጠው መሰረት ሊያቋቅም ይችላል፡፡

### 22. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

በአካባቢ ዘርፍ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ፣ጥናት የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 03/2010 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

### 23. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ድህረ ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 2016

**ሌሊሴ ነሜ ሶሪ**

**የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**

## ዕዝል1
## በልዩ ሁኔታ የሚታዩ የሥራ ልምዶች

1. የአካበቢያዊና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ፣ አካባቢ ኦዲት ሰነዶች ግምገማ ላይ የተሳተፉ፤ በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ አግባብነት ባለው የሥራ መስክ ላይ ስለመስራቱ ማስረጃ የሚያቀርብ እንዲሁም በውጭ አገር በአካባቢ ጥበቃና ተዛማች መስኮች የተሰማሩ ወይም የሰሩ፤

   1.1 የአካበቢያዊና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ሰነዶች ግምገማ፣ አካባቢ ላይ የተሳተፉ፣

      ሀ/ ለጀማሪ ሁለት አመት

      ለ/ ለመካከለኛ ደረጃ ከሶስት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ

      ሐ/ ለከፍተኛ ደረጃ ከአራት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ

   1.2 በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ አግባብነት ባለው የሥራ መስክ የሰሩ

      ሀ/ ለጀማሪ ሶስት አመት

      ሀ/ ለመካከለኛ ደረጃ ከአራት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ

      ለ/ ለከፍተኛ ደረጃ ከአምስት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ

   1.3 በአካባቢ ጥበቃና ተዛማች የሙያ መስኮች ለትዉልደ ኢትዮጵያን ከውጭ አገር የተገኘ የስራ ልምድ

      ሀ/ ለጀማሪ ሶስት አመት

      ለ/ ለመካከለኛ ደረጃ ከአምስት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ

      ሐ/ ለከፍተኛ ደረጃ ከሰበት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ

2. በከፍተኛ የትምህርት እና የምርምር ተቋማት የአካበቢያዊና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ፣የአካባቢ ኦዲት የትምህርት ዓይነትን የሚየስተምሩ የምርምር ስራዎችን የሰሩ ወይም የሚያመክሩ

   ሀ/ ለጀማሪ ደረጃ ሁለት አመት የሰሩ ወይም አንድና ከዚያ በላይ እውቅና የተሰጠው ፅሑፎች ያሳተሙ

   ለ/ ለመካከለኛ ደረጃ ሶስት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ ወይም ሶስትና ከዚያ በላይ እውቅና የተሰጠው ፅሑፎች ያሳተሙ

ሐ/ ለከፍተኛ ደረጃ አምስት አመትና ከዚያ በላይ የሰሩ ወይም አምስትና ከዚያ በላይ እውቅና የተሰጠው ፅሑፎች ያሳተሙ

## ዕዝል 2

## የአካባቢያዊና የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አገልግሎት የሚሰጡ አማካሪ ባለሙያዎች መስፈርት

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የአካባቢ ዘርፍ ጉዳዮች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | አግባቢነት ያለው የስራ ልምድ(በአመት) | ጠቅላለ የሥራ ልምድ (በአመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ ኢኮኖሚያ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በልማት ምጣኔ ሃብት፣በምጣኔ ሃብት፣በግብርና ምጣኔ ሃብት፣የልማት ስራ አመራር፣ አካባቢ ምጣኔ ሃብት፣በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣የግብርና ሃብት ምጣኔ አያያዝ፣አካባቢና ዘላቂ ልማት የቢዝነስ አስተዳደር እና አያያዝ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በልማት ምጣኔ ሃብት፣በምጣኔ ሃብት፣በግብርና ምጣኔ ሃብት፣የልማት ስራ አመራር፣ አካባቢ ምጣኔ ሃብት፣በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣የግብርና ሃብት ምጣኔ አያያዝ፣አካባቢና ዘላቂ ልማት የቢዝነስ አስተዳደር እና አያያዝ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በልማት ምጣኔ ሃብት፣በምጣኔ ሃብት፣በግብርና ምጣኔ ሃብት፣የልማት ስራ አመራር፣ አካባቢ ምጣኔ ሃብት፣በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣የግብርና ሃብት ምጣኔ አያያዝ፣አካባቢና ዘላቂ ልማት የቢዝነስ አስተዳደር እና አያያዝ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |
| 2 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የማህበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በሶሾሎጂ፣ በማህበራዊ ጥናት፣ በልማት ስራ አመራር ፣በህዝብ አያያዝ ጥናት፣ የስራ አመራር፣ በማህበራዊ ስራዎች፣ በማህበራዊ፣ አካባቢና ዘላቂልማት፣ በልማት ጥናቶች፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በሶሾሎጂ፣ በማህበራዊ ጥናት፣ በልማት ስራ አመራር ፣በህዝብ አያያዝ ጥናት፣ የስራ አመራር፣ በማህበራዊ ስራዎች፣ በማህበራዊ፣ አካባቢና ዘላቂልማት፣ በልማት ጥናቶች፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በሶሾሎጂ፣ በማህበራዊ ጥናት፣ በልማት ስራ አመራር ፣በህዝብ አያያዝ ጥናት፣ የስራ አመራር፣ በማህበራዊ ስራዎች፣ በማህበራዊ፣ አካባቢና ዘላቂልማት፣ በልማት ጥናቶች፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |
| 3 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የአካባቢ ጤና ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | የህዝብ ጤና አጠባበቅ፣በአካባቢ ጤና አጠባበቅ አካባቢ ጠና መኮንን፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት፣የአካባቢ ማህበረሰብ ጤንነት፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5 |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የአካባቢ ዘርፍ ጉዳዮች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | አግባቢነት ያለው የስራ ልምድ(በአመት) | ጠቅላላ የሥራ ልምድ (በአመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | የህዝብ ጤና አጠባበቅ፣በአካባቢ ጤና አጠባበቅ አካባቢ ጤና መከንን፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት፣የአካባቢ ማህበረሰብ ጤንነት፣ | •ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | የህዝብ ጤና አጠባበቅ፣በአካባቢ ጤና አጠባበቅ አካባቢ ጤና መከንን፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት፣የአካባቢ ማህበረሰብ ጤንነት፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |
| 4 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የብዝሐ ሕይወት እና የስርዓተ-ምህዳር ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በብዝሃ ሕይወት ጥበቃ፣ በስርዓተ-ምህዳር ጥበቃ/አያያዝ፣ በሥነ-ሕይወት ጥበቃ/አያያዝ፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ በአካባቢ እና ዘላቂ ልማት፣ በግብርና ኢኮሎጂ ፣በኢኮሎጂ፣ በተፋሰስ ልማት ወይም አያያዝ፣ ፣በደን አያያዝ እና እቅድ፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በብዝሃ ሕይወት ጥበቃ፣ በስርዓተ-ምህዳር ጥበቃ/አያያዝ፣ በሥነ-ሕይወት ጥበቃ/አያያዝ፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ በአካባቢ እና ዘላቂ ልማት፣ በግብርና ኢኮሎጂ ፣በኢኮሎጂ፣ በተፋሰስ ልማት ወይም አያያዝ፣ ፣በደን አያያዝ እና እቅድ፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በብዝሃ ሕይወት ጥበቃ፣ በስርዓተ-ምህዳር ጥበቃ/አያያዝ፣ በሥነ-ሕይወት ጥበቃ/አያያዝ፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ በአካባቢ እና ዘላቂ ልማት፣ በግብርና ኢኮሎጂ ፣በኢኮሎጂ፣ በተፋሰስ ልማት ወይም አያያዝ፣ ፣በደን አያያዝ እና እቅድ፣ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |
| 5 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የውሃ እና የሃይል አጠቃቀም አጥኚ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በውሃ ሀብት አሰተዳደር ወይም አጠቃቀም፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የውሃ ምህንድስ፣/የከርሰ ምድር ጥናት፣ በሀይድሮልክ ምህንድስና፣ በጂኦሎጅ በሃይድሮጂኦሎጅ ፣በአፈረና ውሃ ጥበቃ፣ በአፈር እና ውሃ ምንድስና፣ በመስኖ ምህንድስና በተፋሰስ አያያዝ፣ በውሃ አዘል መሬቶች አያያዝ እና አጠቃቀም | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በውሃ ሀብት አሰተዳደር ወይም አጠቃቀም፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የውሃ ምህንድስ፣/የከርሰ ምድር ጥናት፣ በሀይድሮልክ ምህንድስና፣ በጂኦሎጅ በሃይድሮጂኦሎጅ ፣በአፈረና ውሃ ጥበቃ፣ በአፈር እና ውሃ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የአካባቢ ዘርፍ ጉዳዮች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | አግባቢነት ያለው የስራ ልምድ(በአመት) | ጠቅላለ የሥራ ልምድ (በአመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ምንድስና፣ በመስኖ ምህንድስና በተፋሰስ አያያዝ፣ በውሃ አዘል መሬቶች አያያዝ እና አጠቃቀም | | |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በውሃ ሀብት አሰተዳደር ወይም አጠቃቀም፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የውሃ ምህንድስ፣/የከርሰ ምድር ጥናት፣ በሀይድሮልክ ምህንድስና፣ በጂኦሎጅ በሃይድሮጂኦሎጅ ፣በአፈረና ውሃ ጥበቃ፣ በአፈር እና ውሃ ምንድስና፣ በመስኖ ምህንድስና በተፋሰስ አያያዝ፣ በውሃ አዘል መሬቶች አያያዝ እና አጠቃቀም | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |
| 6 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የአካባቢ ብክለት ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በአካባቢ መንሀንዲስና ፣ ኬሚካል መሃንዲስ፣ በአካባቢ አያያዝ ወይም አስተዳደር፣በተፈጥሮ ሃብት አያዝ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ፣ በአካባቢና ዘላቂ ልማት፣ በአፈር ውሃ ምህንድስና፣ በውሃ ምህንድስና ሂድሮሎጂ ምህንድስና | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በአካባቢ መንሀንዲስና ፣ ኬሚካል መሃንዲስ፣ በአካባቢ አያያዝ ወይም አስተዳደር፣በተፈጥሮ ሃብት አያዝ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ፣ በአካባቢና ዘላቂ ልማት፣ በአፈር ውሃ ምህንድስና፣ በውሃ ምህንድስና ሂድሮሎጂ ምህንድስና | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በአካባቢ መንሀንዲስና ፣ ኬሚካል መሃንዲስ፣ በአካባቢ አያያዝ ወይም አስተዳደር፣በተፈጥሮ ሃብት አያዝ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ፣ በአካባቢና ዘላቂ ልማት፣ በአፈር ውሃ ምህንድስና፣ በውሃ ምህንድስና ሂድሮሎጂ ምህንድስና | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |
| 7 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ አየር ንብረት ለውጥ ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በአየር ንብረት ለውጥ አካባቢ ሳይንስ፣የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ፣ በኬሚስትሪ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ አካባቢና ዘላቂ ልማት፣ከተማ አያየዝ አየር ንብረት ለውጥ አያያዝ፣ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ የአካባቢ ህግ አካባቢ ፖሊሲ፣ አፕላይድ ኢኮሎጂ፣ አየር ንብረት ለውጥ ስርይት ማጣጣምያ፣ በአካባቢ ጤና | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 0<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 0<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በአየር ንብረት ለውጥ አካባቢ ሳይንስ፣የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ፣ በኬሚስትሪ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ አካባቢና ዘላቂ ልማት፣ከተማ አያየዝ አየር ንብረት ለውጥ አያያዝ፣ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ የአካባቢ ህግ አካባቢ | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡1<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡0 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የአካባቢ ዘርፍ ጉዳዮች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | አግባቢነት ያለው የስራ ልምድ(በአመት) | ጠቅላለ የሥራ ልምድ (በአመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፖሊሲ፣ አፕላይድ ኢኮሎጂ፣ አየር ንብረት ለውጥ ስርይት ማጣጣምያ፣ በአካባቢ ጤና | | |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በአየር ንብረት ለውጥ አካባቢ ሳይንስ፣የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ፣ በኬሚስትሪ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ አካባቢና ዘላቂ ልማት፣ከተማ አያየዝ አየር ንብረት ለውጥ አያያዝ፣ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ የአካባቢ ህግ አካባቢ ፖሊሲ፣ አፕላይድ ኢኮሎጂ፣ አየር ንብረት ለውጥ ስርይት ማጣጣምያ፣ በአካባቢ ጤና | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 3<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 2<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡1 | •ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 10<br>•ለሁለተኛ ድግሪ፡ 7<br>•ለዶክተሬት ድግሪ፡ 5 |

*በዚህ ዕዝል የተጠቀሰው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ እና የአካባቢ ኦዲትን ጥናትን ያካትታል፡፡*

## ዕዝል 3

## በአካባቢያዊና የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አገልግሎት የሚሰጡ አማካሪ ድርጅቶች መስፈርት

| ተ.ቁ | ለአማካሪው ድርጅት የሚሰጠው ደረጃ | አማካሪው ድርጅት የሚያስፈልጉት ባለሙያዎች | | | የሚሰማራባቸው የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ጥናት መስኮች | ሌሎች መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝርዝር | የሙያ ደረጃ | ብዛት | | |
| 1 | I | የኢኮኖሚያ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካካሪ | 1 | ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው ፕሮጅክቶች እና ስክኬጂውል 1 ውስጥ የተካተቱ ፕሮጅክቶች ዝርዝር የሚያከናውን<br>• የኢንዱስትሪ ዞን ምስረታ<br>• የሀይድሮፓወር ግድብ ግንበታ(ሁሉንም ከፍታና ኃይል ማመንጨት )<br>• የመስኖ/የሰብል ልማት<br>• የባቡር ግንባታ<br>• ሁሉንም የትራፊክ ፍሰቱ ከፍተኛ የሆነ የመንገድ ግንባታ እንዲሁም ነባር መንገዶችን ማስፋፋት/ማሻሻል<br>• የኬሚካል ማምረቻ ፋብሪክ<br>• የነዳጅ ማከማቻ ግንባታ<br>• የአለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ቦታ ግንባታ<br>• የነዳጅ እና የወርቅ ማዕድን ማውጣት<br>• የቆሻሻ ማስወገጃ/ማከሚያ ግንባታ<br>• በጥብቅ ስፍራ የሚካሄዱ ልማቶች<br>• አባወራዎች የሚፈናቀሉባቸው የልማት ፕሮጀክቶች<br>• ልውጠ ህያውና የውጭ ዝሪያዎችን የሚጠቀሙ የልማት ፕሮጀክቶች<br>• የከርሰ ምድር ውሃ ልማት<br>• ዘመናዊ የአሣ እርባታ<br>• የሥርዓተ-መሀድር አጠቃቀም ለውጥ<br>• አበባ ልማት<br>• የጎማ ፋብሪካ<br>• የሲሚንቶ ፋብሪካ<br>• የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ<br>• የቆዳ ማልፋት ፋብሪካ<br>• የብረታ ብረት ማቅለጫና ማምረቻ ፋብሪካ<br>• የወረቀት ፋብሪካ | • ስራ አስኪያጁን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት ቋሚ ሰራተኞች<br>• መነሻ ካፒታል ቢያንስ 200 ሺ ብር<br>• የመስሪያ ቦታ/ቢሮ ቢያንስ 20 ካሬ ሜትር<br>• የቢሮ የጽህፈት መሳሪያዎች/ኮምፒዩተሮች |
| | | የማህበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የአካባቢ ጤና ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | አየር ንብረት ለውጥ ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የብዝሐ ሕይወት እና የስርዓተ-ምህዳር ተንታኝ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የውሃ/ተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የአካባቢ ብክለት ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |

| ተ.ቁ | ለአማካሪው ድርጅት የሚሰጠው ደረጃ | አማካሪው ድርጅት የሚያስፈልጉት ባለሙያዎች | | | የሚሰማራባቸው የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ጥናት መስኮች | ሌሎች መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝርዝር | የሙያ ደረጃ | ብዛት | | |
| | | | | | • የምግብ/የመጠጥ ፋብሪካ<br>• የሆስፒታል ፋብሪካ<br>• የቄራ ግንባታ<br>• የድንጋይ ከሰል/ጂኦተርማል/ንፋስ ኃይል ማንመንጫ ግንባታ<br>• የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የውሃ ማከሚያ ፕላንት ግንባታ<br>• የመንግስት ሰነዶች/ፖሊሲዎች፣ ፕላኖች፣ ፕሮግራሞች<br>• የስደተኞች ካምፕ ምስረታ<br>• ለውሃ አቅርቦት የሚገነባ - ግድብ (100 ሄክ)<br>• የዱር እንስሳት እርባታ<br>• ተራራማና ኮረብታማ አካባቢዎች የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች | |
| 2 | II | የኢኮኖሚያ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | 1 | ከስኬጀውል ሁለት ያሉትን ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናትን ያከናውናል<br>• የጋራ መኖሪያቤቶች ግንባታ<br>• የሰብል ልማት (ከ1000 ሄክታር በታች)<br>• የኃይል መስመር ግንባታ<br>• የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት<br>• የእንስሳት ማድለብ<br>• የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የውሃ ማከሚያ ፕላንት ግንባታ<br>• የንብ እርባታ<br>• የገጠር መንገዶች ግንባታ<br>• ጋራዥ<br>• የከተማ ግብርና<br>• የአካባቢና የማህበረሰብ አያያዝ እቅድ ዝግጅት | • ስራ አስኪያጁን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት ቋሚ ሰራተኞች<br>• መነሻ ካፒታል ቢያንስ 150 ሺ ብር<br>• የመስሪያ ቦታ/ቢሮ ቢያንሰ 15 ካሬ ሜትር<br>• የቢሮ የጽህፈት መሳሪያዎች/ኮምፒዩተሮች |